13 ኛ ዓመት ቁጥር 7
13th Year No 7

ባህር ዳር መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 154/2000 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣውን አወጅ እንደገና ማሻሻያ አወጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት
የወጣ

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.95
Unit price ------

### አዋጅ ቁጥር 154/2000 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ለብሔራዊ ክልሉ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ኘሮግራም ውጤታማነት የሚያግዙ አደረጃጀቶች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዘርጋታቸውና በእነዚህ አደረጃጀቶች ውስጥም የሚመደቡ ኃላፊዎችን ብቃት እየመረመረ መርጦ የሚሾም ተቋም በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

ይህንን ኃላፊነትም ለክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በአዋጅ መስጠቱ እንደሚጠቅም በመታመኑ፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ- መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጀል፡፡

**1.** <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ" የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ እንደገና

ለማሻሻል የወጣ አወጅ ቁጥር 154/2000 ዓ.ም “ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.** ማሻሻያ

የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

1. የጠቅላይ ፍ/ቤቱን የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ፣ ጥናትና ሥልጠና ጽ/ቤት ኃላፊን እና የፍርድ መርማሪና ኢንስፔክተር፤ እንዲሁም ሬጅስትራሮችንና ተከላከይ ጠበቆችን መርጦ ይሾማል፤ ይመድባል፤ የደመወዝና እነርሱን የሚመለከተቱ ሌሎች ተዛማጅ የአስተዳደር ጉደዩችን መርምሮ ይወሰናል፤ እንደአስፈላጊነቱም የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**3.** አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አወጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

መጋቢት **15** ቀን **2000** ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት